# ምዕራፍ 4

## ለምን እንደምናመልክ ማወቅ

1. እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነ እናመልከዋለን። አምልኮ የሚለው ቃል ሥረ አመጣጡ አምላክ ከሚለው ቃል ነው። ስለዚህም ይህ ቃል አምላክ ከሚለው ቃል ሲፈልስ እግዚአብሔር አምልኮ የሚገባው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ማሳየቱን ልብ ልንል ይገባል። አምልኮ ከአምላክ ጋር የተያያዘ ቃል ነው። እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነ አምልኮ ይገባዋል።

2. ፍጥረቱ ስለሆንን እናመልከዋለን። እግዚአብሔር እኔና እናንተን የፈጠረን ለራሳችንም ለዓለምም ሳይሆን እርሱን እንድናመልክ ነው።

3. በክርስቶስ ስለዳንን እናመልከዋለን። በደሙ ያጠበንና የቀደሰን በጌታ ኢየሱስ አማካይነት እግዚአብሔር አብን እንድናመልከው ነው።

4. መንፈስ ቅዱስ ስለ ተሰጠን እናመልከዋለን። በበዓለ ሃምሳ ቀንም መንፈስ ቅዱስ የመጣው እግዚአብሔርን ለማምለክ እንዲረዳን ነው። ከአምላካችን ጋር ተቋርጦ የነበረውን አንድነት

መንፈስ ቅዱስን በመላክ ያደሰው እግዚአብሔርን ማምለክ እንድንችል ነው።

5. **ትዕዛዝ ስለሆነ እናመልከዋለን።** (1ዜና 16፡29፤ መዝ. 94፡6፤ መዝ. 95፡9፤ ራዕይ 22፡9፤) እግዚአብሔርን ማምለክ ከሁሉ በላይ የከበረ አገልግሎት ስለሆነ እናመልከዋለን። የከበረ አገልግሎት ምንድነው? ለእግዚአብሔርስ የምናቀርብለት ምንድነው? ብለን ለምንጠይቅ ለእግዚአብሔር በቀጥታ የምናቀርብለት ነገር ቢኖር አምልኮ ብቻ ነው። የከበረ አገልግሎትም እግዚአብሔርን በእውነት ማምለክ ነው። በእርሱ ፊት ወድቀን ስንሰግድለት ያን ጊዜ ለእርሱ አምልኮን እናቀርብለታለን። መታዘዛችንን የምናሳየው እግዚአብሔርን በማምለክ ነው።

6. **እግዚአብሔር የሚፈልገው ስለሆነ እናመልከዋለን።** "ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤" (ዮሐ. 4:23)

7. **የፍቅራችን መግለጫ ስለሆነ እናመልከዋለን።** አምልኮ የፍቅር፣ የምስጋናና የውዳሴ መግለጫ ነው። እግዚአብሔር ላደረገልን ነገር ሌላ መግለጫ የለንም። ስለዚህ ፍቅራችንን የምንገልጸው በአምልኮ ነው።

8. **በአምልኮ ውስጥ ፍጹም እርካታ ስላለ እናመልከዋለን።** ነፍሳችን የምትረካው በእውነተኛ አምልኮ ውስጥ ብቻ ነው። ዳዊት በመዝሙሩ ይህን ሲገልጽ እንዲህ ይላል።

"እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ፣ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ፣ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ።" (መዝ. 26:4) "ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ፤ አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ አንተ እጅግ ታላቅ ነህ፤ ክብርንና ግርማን ለበስህ። ብርሃንን እንደ ልብስ ለበስህ፤ ሰማይን እንደ መጋረጃ ዘረጋህ፤" (መዝ. 103:1-2)

9. **እውነተኛ ለውጥ ስለምናገኝ እናመልከዋለን።** በአምልኮ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርበን ከእርሱ ጋር ከተነጋገርን እውነተኛ ለውጥ ይኖራል። "... ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለተነጋገረ የፊቱ ቊርበት እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር።" (ዘጸ. 34:29)

10. **የእግዚአብሔርን ድምጽ ስለምንሰማ እናመልከዋለን።** "እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ:- በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።" (ሐዋ. 13:2)

11. **እውነተኛ ደስታን ስለምናገኝ እናመልከዋለን።** "እነርሱም፤ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፣ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ።" (ሉቃ. 24:52) "እነሆም:- ኢየሱስ አገኛቸውና:- ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።" (ማቴ. 28:9)

12. አምልኮ በሕይወታችን ውስጥ የሚያፈራው ፍሬ ስላለ እናመልከዋለን። እውነተኛና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የአምልኮ ሕይወት ታላቅ በረከት ያመጣል። እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ስናመልክ በሕይወታችን ውስጥ ከሚፈጸሙት ነገሮች ውስጥ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል:-

- እግዚአብሔር አምላክ የሚገባውን ምስጋና ይቀበላል። እርሱ በሰማይና በምድር ብቻ ሳይሆን በሕይወታችንም ውስጥ ይከብራል። (ሉቃ. 2:14)
- ታላቅ መንፈሳዊ እርካታና ደስታ ይሰጣል። (ሉቃ. 24:51)
- እግዚአብሔርን በጠለቀና በከፍተኛ ደረጃ ማወቅ ያስችላል።
- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት ያስችላል። (ሐዋ. 13:2)
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመለየት ያስችላል። (ሐዋ. 13:2)
- የጸሎት ሕይወትን ያድሳል።
- በምስጋና ሕይወት ስለሚሞላ የምሕረቱን ብዛት ለማስተዋል ይረዳል። (መዝ. 135)
- ቅድስናውን፣ ውበቱንና ፍቅሩን ለመረዳት ያስችላል።
- የእግዚአብሔር ሕልውና ሕይወትን፣ አመለካከትን፣ አኗኗርን፣ ስሜትንና የውስጥ ፍላጎትን ይለውጣል።
- እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ያሳድጋል።
- መንፈሳዊ ተሃድሶን ያመጣል። (2ዜና. 29)
- የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ ያደርጋል። (2ዜና. 7:1-3)
- ድልን ያጎናጽፋል። (2ዜና.20፤ ሐዋ. 16:25-29)
- በረከትና ፈውስን ይሰጣል። "አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ታመልኩታላችሁ፣ እርሱም እህልህንና ውኃህን ይባርካል፤ በሽታንም ከመካከልህ አርቃለሁ፤" (ዘጸ. 23:25)

# በምን እንደምናመልክ ማወቅ

1. በሕይወታችን እናመልከዋለን። ማርያም «የእግዚአብሔር ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» በማለት ሕይወቷን ሰጠች። (ሉቃስ 1፥38) በኑሮአችን እናመልከዋለን። የምንኖረው ኑሮ አምልኮአችንን የሚገልጽ መሆን አለበት። ምን ዓይነት ኑሮ ነው የምንኖረው? ምን ዓይነት አነጋገር ነው የምንናገረው? አካሄዳችን ምን ዓይነት ነው? የሕይወታችን ቅድስና ምን ይመስላል? እነኝህ ሁሉ የአምልኮአችን መግለጫዎች ናቸው። የአምላካችንን ታላቅነት የሚያሳዩ ናቸው። ሕይወታችንን ማን እንደሚገዛው፤ ሕይወታችን በማን ቁጥጥር ስር እንደሆነ የምናሳየው በምንኖረው ኑሮ ነው። የእግዚአብሔር ቃል «ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና።» (2ኛጴጥ. 2፥19) ይላል። ስለዚህ የተሸነፍንለትን (የተንበረከክንለትን) ነገር ነው የምናመልከው። ስለሆነም የምንገዛለት፤ የምንበረከክለት "ይህ ካልሆነ አይሆንም" የምንላቸው ነገሮች ሁሉ ለአምልኮ ጠንቅ ናቸው። ካልተጠነቀቅን አገልግሎትም ቢሆን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ይገባና ከእግዚአብሔር ይልቅ አገልግሎትን ማምለክ እንጀምራለን። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለክብሩ የሰጠንም ስጦታ አምላክ (ጣዖት) ይሆንብናል። ሰው ከፍተኛው የሕይወት ጥሪው እግዚአብሔርን ማምለክ ከሆነ ለምን ከሌላ ጋር ይጋፋል? አምልኮ ደግሞ እውነተኛ አገልግሎት ከሆነ፣ አገልግሎታችን አምላክ እንዲሆንብን አያስፈልግም። ጌታ ሕይወታችንን የዋጀው ለአገልግሎት አይደለም እርሱን እንድናመልከው ነው። እያንዳንዳችን በግላችን ወደዚህ መረዳት ለመድረስ መጣጣር ያስፈልገናል። ከመስበካችንም በፊት፣ ከማስተማራችንም በፊት ጥማታችን አምላካችንን ማወቃችንና እርሱን እንደሚገባው

ማምለካችን መሆን አለበት። የሕይወታችን ዓላማ ለእርሱ መኖራችን፣ እርሱን ማስከበራችንና ከፍ ከፍ ማድረጋችን፣ ነፍሳት ሲድኑና ቅዱሳን ሲታነጹ ማየታችን መሆን አለበት። ከዚህ የበለጠ ደስታ የሚሰጠን የግል አገልግሎታችን ከሆነ ራሳችንን እንመርምር። ወገኖቼ! እግዚአብሔር ከከበረ፤ ኢየሱስ ከከበረ፤ እግዚአብሔር ከተመለከ ይበቃናል። ሰዎች ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር እርሱ ጌታ መሆኑን ካወቁ ይበቃናል።

በኑሮአችንና በአንደበታችን እግዚአብሔርን እናምልከው። በዚህ ሕይወቱ አስገራሚ ልምምድ ያለው ዳዊት የአንደበታችሁን ምስጋና አቅርቡ በማለት እኛን ከመቀስቀሱም በላይ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት በአንደበቱ በቅኔ፤ በውዳሴና በዝማሬ ያመልክ የነበረ የእግዚአብሔር ሰው ነው።

2. በጸጋ ስጦታዎች እግዚአብሔርን ማመለክ አለብን። የሚሰጡን የጸጋ ስጦታዎች ምንም ዓይነት ቢሆኑም ለእግዚአብሔር አምልኮ መዋል አለባቸው። ሰብአ ሰገል ያደረጉት ያንን ነው። "እነሆ ሰብአ ሰገል፡- የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና በማለት ከምሥራቅ አገር ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ... ወደ ቤትም ገብተው ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት ወድቀውም ሰገዱለት፣ ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት።" (ማቴ. 2:2፣11) ስጦታቸውን ይዘው ለንጉሡ ልንሰግድለት መጥተናል አሉ። የእነርሱን ሕይወት ስናይ እንዴት ደስ ያሰኛል። ሀብታሞች ናቸው ወርቅ ይዘው መጥተዋል። ነገር ግን ወርቅ ልንሰጠው መጥተናል ሳይሆን ልንሰግድለት መጥተናል አሉ። ኢየሱስ የሚፈልገው ወርቁን አልነበረም። ወርቁና ብሩም የእርሱ ነው። ሁሉ ያለውን አምላክ ልናመልከው መጥተናል

ስጦታዎች ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ማወቅና እርሱን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማምለክ ብንችል እንዴት ድንቅ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች በሚገለጡበት ጊዜ የሚያስፈራ ነገር ሊታይ ይችላል። ይኸውም ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ የጸጋ ስጦታን ማምለክ ስለሚቃጣቸው ነው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ይልቅ በጸጋ ስጦታዎች ላይ ያላቸው ፍላጎት እየመዘነ ይሄዳል። ግን የስጦታውን ያህል እግዚአብሔርን ፈልገነው ቢሆን ኖሮ፣ ለእርሱ ያንን ያህል ተሰጥተን ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ምን ያህል ድንቅ ነገር ማድረግ በቻለ!

3. በመታዘዛችን እናመልከዋለን፤ እግዚአብሔርን ፈቃዱን በመጠበቅ እናመልከዋለን። ፈቃዱን ለመጠበቅ የሚያስቸግራችሁ ሰዎች ሉቃስ 2፥25–32 አንብቡ። ስምዖን የሚባለው ሰው እግዚአብሔርን ያመለከው የእግዚአብሔርን ቀን (ጊዜ) በመጠበቁ ነው። እግዚአብሔርም በጊዜው እራሱን ገለጠለት። እርሱም ሕጻኑን ጌታ ኢየሱስን በማየቱ ረክቶ ዕድሜም ቢሆን በቃኝ አለ። የእግዚአብሔርን ጊዜ በመጠበቅ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደምንችል የስምዖን ሕይወት ትልቅ ምሳሌያችን ነው።

4. በገንዘባችን እናመልከዋለን። እግዚአብሔር ከሰጠን መልሰን ለእርሱ ሥራ በመስጠት አምልኮአችንን እንገልጻለን። ሰብአ ሰገል ውድ የሆነውን ስጦታቸውን ወርቅ፣ ከርቤና እጣን በማቅረብ አምልኮአቸውን ገለጹ። በአሥራታችን እግዚአብሔርን እናመልከዋለን። ከተሰጠን ሁሉ ከአሥሩ እጅ አንዱ የእርሱ ነው። እርሱን አለመስጠት ለአምልኮ እንቅፋት ይሆናል። በፍቅር ስጦታችንም እናመልከዋለን። ጌታ ስጥ ሲለን በደስታ ለእርሱ ሥራ ስንሰጥ እርሱ ያከብራል።

# እንዴት እንደምናመልክ ማወቅ

እግዚአብሔርን በቤተክርስቲያን (በጉባኤ)፤ በቤተሰብ፤ በግለሰብ ደረጃ እናመልከዋለን። ከአንደበታችን በሚወጡት በዝማሬ፤ በምስጋና፤ በእልልታ፤ በቅኔና እንዲሁም በጸጥታ እናመልከዋለን። እነዚህ ሁሉ የአምልኮ መግለጫዎች ናቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ ከአንደበታችን በሚወጡት በዝማሬ፤ በምስጋና፤ በእልልታና በቅኔ እግዚአብሔርን እናመልከዋለን። እግዚአብሔር ታላቅነቱን በሚያሳየን ጊዜ በፊቱ እንዘምራለን፤ እንዘላለን፤ በምስጋና በፊቱ እንቀርባለን። አምልኮአችንን እንገልጻለን። አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎችን አፍስሶ ሰዎች መንፈሳቸው በሚነቃቃበት ጊዜ አምልኮ ያ ብቻ ይመስለናል። በሌላ ጊዜ ደግሞ መዝሙር በሚዘመርበት ጊዜ ካልዘለልኩ፣ ወይም ስሜቴን በጣም ደስ ካላለው እግዚአብሔርን አላመለኩም ብለን አዝነን እንተወዋለን። ያ ግን የአምልኮ መግለጫ መንገድ ብቻ ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ ግን ፎርሙላ የለውም። የምንሳሳተው ለአምልኮ ስልት ስናወጣለት ነው። እግዚአብሔርን አይቶ እንዲህ ልዘምርለት ወይም የእግዚአብሔርን ታላቅነት አስተውሎ እዚያ ቆሞ የአምልኮ ፎርሙላ (ስልት) የሚያወጣ የለም። እግዚአብሔርን ስናይ መዝለል ካስፈለገ እንዘላለን፤ በፊቱ በቅዱስ ግርማው መውደቅ ካስፈለገ እንወድቃለን፤ ጸጥ ማለት ካስፈለገ ጸጥ እንላለን። እነዚህ ሁሉ አምልኮዎች ናቸው። አምልኮን አምልኮ የሚያደርገው አካላዊ ድርጊቱ ሳይሆን ማንን ነው የምናመልከው? ክብርን ለማን ነው የምንሰጠው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለራሳችን በትክክል ከመለስን ነው። ጥቂት ሰዎችን ለምሳሌ እንጥቀስ፦

▶ **አብርሃም**፦ እግዚአብሔርን ያመለከው አንድ የሚወደውን ልጁን መሥዋዕት ለማድረግ በታዛዥነት በማቅረብ ነበር። «... አብርሃምም በዚያ መሠዊያ ሠራ እንጨትም ረበረበ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያም እንጨት ላይ አጋደመው። አብርሃምም እጁን ዘረጋ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ።» (ዘፍ. 22፡9–10) ይህ የመታዘዝ አምልኮ ነው። ነገር ግን ሰው ሁሉ ልጁን በመሠዊያ ላይ ማድረግ አለበት ማለት አይደለም።

▶ **ሙሴ**፦ እግዚአብሔርን ያመለከው ፊቱን በመሸፈንና ጫማውን በማውለቅ ነበር። «ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።» (ዘፀ. 3፡5–6) አክብሮትንና ቅድስናን የሚያመለክቱ ድርጊቶች ናቸው። ጫማችንን ማውለቅና ፊታችንን መሸፈን ግን አምላኪዎች ያደርገናል ማለት አይደለም።

▶ **ዳዊት**፦ የተማረከው የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ከተማይቱ በመለሰ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ዘለለ። ሚስቱ ሚልኮል እስክትንቀው ድረስ ሐሴት አደረገ። «...ንጉሡም ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልልና ሲዘፍን አየች በልብዋም ናቀችው።» (2ሳሙ. 6፡16) ዳዊት የአምላኩን ታቦት ስላየ የራሱን ክብር ትቶ ለአምላኩ ያለውን አክብሮትና ፍቅር እየዘለለ ገለጠ፤ አምልኮው ያተኮረው መዝለሉ ላይ ሳይሆን ያዘለለው ነገር ላይ ነበር።

▶ **ማርያም** (የሙሴ እህት)፦ እግዚአብሔርን ያመለከችው በመዝሙርና በከበሮ ነው። «የአሮን እህት ነቢይቱ ማርያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን ከኋላዋ ወጡ። ማርያምም እየዘመረች መለሰችላቸው፦ በክብር ከፍ

ብሏልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ።» (ዘፀ. 15፡20-21) እያለች ታምራቱን በማስተዋል አመሰገነች (አመለከች)። አሁንም አምልኮ የሚያደርገው ክብሮ የሚያስመታ ምክንያት መኖሩ ነው እንጂ ክብሮ መመታት አይደለም።

▶ **ዳንኤል**፡- እግዚአብሔርን ያመልክ የነበረው በተወሰነ ሰዓት በፊቱ ተንበርክኮ እጆቹን ወደ አምላኩ በማንሣት ነበር። «...ቀድሞ ያደርግ እንደነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት ጸለየ። አመሰገነም።» (ዳን. 6፡10)

▶ **ሰብአ ሰገል**፡- ጌታን ያመለኩት በፊቱ በመውደቅ ነበር። «ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት ወድቀውም ሰገዱለት...» (ማቴ. 2፡11)

▶ **ሐዋርያው ዮሐንስ**፡- ጌታ ኢየሱስን ባየው ጊዜ የሰገደለት በመዘመር፤ በመዝለልም አልነበረም። ጸጥ ብሎ በፊቱ በመውደቅ ነው። «ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ» ይላል። ህዋሳቱም መንቀሳቀስ አልቻሉም። (ራዕይ 1፡10)

▶ **ማርያም መግደላዊት** ሌሎችም ሰዎች፡- ያመለኩት በታላቅ ደስታ በእግሩ ሥር በመውደቅ ነበር። «እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።» (ማቴ. 28፡9)

▶ **ቶማስ**፡- ጌታን «ጌታዬ አምላኬም...» ብሎ በፊቱ በመውደቅ ነበር ያመለከው። (ዮሐ. 20፡28)

▶ ሐዋርያት፦ ያመለኩት በስግደት ነበር። «እነርሱም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።» (ሉቃስ 24፡51)

የእነዚህና የሌሎች ቅዱሳን አምልኮ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ነበረው። የአመላለካቸው ዘዴና ሁኔታ ግን በጣም የተለያየ ነበር። ለአምልኮአቸው ተቀባይነት የሰጠው ሥርዓቱ ሳይሆን በእውነት ላይ ቆመው በመንፈስ ሆነው በቅድስና፣ በቅዱስ ፍርሃትና በአክብሮት በታዛዥ ልብ አምላካቸውን ማምለካቸው ነው። በእውነት የሆነ አምልኮ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ማስመሰል የሌለበት ሲሆን የሚቆጣጠረው የሰዎች ሁኔታ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ የእውነተኛ አምልኮ ጥያቄ ሁልጊዜ: እንደ ማን ወይም እንደነማን ላምልክ ሳይሆን «ማንን ነው የማመልከው?» የሚል መሆን አለበት። አምልኮአችን አካባቢያችንን በማየት ሳይሆን አምላካችንን ለማየት መሆን አለበት።

ሰዎች ለአምልኮ ወግና ሥርዓት ሲያወጡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይወጣሉ። አምልኮ እግዚአብሔርን ማየት ነው። እንግዲህ ብንዘል ለምንድነው የምንዘለው? ዝም ብንል ለምንድነው ዝም የምንለው? መንፈሳዊ ለመምሰል ነውን? ወይስ ደግሞ እግዚአብሔርን አይተን ነው? የምናደርገውን ሁሉ የምናደርገው ስለምንድነው? የሚለውን ሃሳብ ጠንቅቆ ማወቅ በመንፈስ የተጀመረው አምልኮ በሥጋ ስሜት ብቻ እንዳይመራ ለመጠበቅ ይጠቅማል። አምልኮ በሕይወታችን ውስጥ የሚሆነውን ነገር መግለጫ መንገድ እንጂ የሥጋን ስሜት ማርኪያ ልምምድ አይደለም።

# ም ዕ ራ ፍ 5

◊

## የግል አምልኮ

የግለሰብ የአምልኮ ጊዜ በግላችን እንደ ልጅ ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ነው። የግል ወይም እያንዳንዳችን ለብቻችን ከእግዚአብሔር ጋር የምንሆንበት ጊዜ ማለት ነው። ይህ የግል የአምልኮ ጊዜ የምስጋና፣ የጥያቄ፣ የመውደድና የማመስገን ጊዜ ነው። የልባችንን ለአምላካችን የምንነግርበት ጊዜ፣ በጸጥታ ፍቅሩን፣ ምሕረቱን፣ ቸርነቱን፣ ወዘተ. የምንለማመድበት የምናሰላስልበት ሰዓት ነው። ይህ የግል አምልኮ ጊዜ ከራሳችን አልፈን በመጀመሪያ ደረጃ ለእግዚአብሔር ለታላቅነቱ፣ ለቅድስናውና ለግርማው የምንገዛበትና የልቡን አሳብ የምንረዳበት ሰዓት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሔር በውስጣቸው አልፎ ለሌሎች በረከት ያደረጋቸው ሰዎች አሉ። እነዚህም ሰዎች ሳያቋርጡ በግላቸው እግዚአብሔርን ማምለክ ያዘወተሩ ሰዎች እንደ ነበሩ እናስተውላለን። ለምሳሌ ያህል፦

1. **ኖህ**፦ ብቻውን እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሚያመልክ ሰው ነበር። «ኖህም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ፣ ኖህ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።» (ዘፍ. 6፡9) አምላኩን በግል ስለ ተለማመደ አካሄዱን ከእርሱ ጋር በማድረግ ከዘመኑ

ከፋትና ኃጢአት መለየትና በትዕግሥት እግዚአብሔርን መታዘዝ አልከበደውም። በግል የተለማመደውን በአደባባይ በገሐድ ኖረው። ስለዚህም የእግዚአብሔር የሃሳቡ ተካፋይ የእቅዱም ምስጢር የተገለጠለት ሰው ሆነ።

2. **ሄኖክ፡-** በግል የእግዚአብሔር ጓደኛና ወዳጅ ነበረ። «ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና።» (ዘፍ. 5፡24) ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው። በኖረበት በሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ውስጥ እግዚአብሔርን በግል ማምለክ ተማረ። ከአምላኩ ጋር በዋለ ቁጥር እርሱን እየመሰለ ሄደ፤ በመጨረሻም የሚያመልከው ጌታ በዚያው እንደ ወሰደው ተመስክሮለታል። የግል አምልኮ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ይለውጣልና።

3. **አብርሃም፡-** በግሉ እግዚአብሔርን በማምለክ የኖረ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር ሲመሰክርለት ወዳጄ ብሎታል። «አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ። የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።» (ያዕ. 2፡23) በግል አብረው የማይሆኑ የማይለማመዱ ሰዎች ወዳጅነታቸው ጠንካራ እንደማይሆን የታወቀ ነገር ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን ከአገሩ፤ ከብሔሩና ከአባቱ ቤት ለይቶ ለዓለም ሁሉ በረከት ያደረገው ብቻውን በአምላኩ ፊት መቆም ስለ ተለማመደ ነበር። "... አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር።" (ዘፍ. 18: 22) "ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፣ ወደ ወለደቻችሁም

ወደ ሣራ ተመልከቱ፤ አንድ ብቻውን በሆነ ጊዜ ጠራሁት፣ ባረክሁትም አበዛሁትም።” (ኢ.ሳ. 51:2)

4. **ያዕቆብ**:- የተመኘውንና ለብዙ ዘመን ሲፈልግ የነበረውን በረከት ከመቀበል አልፎ እግዚአብሔርን ማየቱን የመሰከረው ብቻውን በነበረበት ጊዜ ነበር። “ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፤ አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር።” (ዘፍ. 32:24) «ያዕቆብም እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው።» (ዘፍ. 32፡30) “ያዕቆብም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን ያን ቦታ ቤቴል ብሎ ጠራው።” (ዘፍ. 35፡15) “ያዕቆብም ከእንቅልፉ ተነሥቶ:- በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው፤ እኔ አላወቅሁም ነበር አለ።” (ዘፍ. 28፡16)

5. **ኢሳያይስ**:- የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ ብቻውን ከአምላኩ ጋር እንደ ነበረ እንረዳለን። (ኢሳይያስ 6፡1–8)

6. **ዳንኤል**:- በግል ጊዜ ወስኖ አምላኩን የሚያመልክ ሰው ነበር። «...ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ አመሰገነም። እነዚያም ሰዎች ተሰብስበው ዳንኤል በአምላኩ ፊት ሲጸልይና ሲለምን አገኙት።» (ዳን. 6፡10–11) ከግል አምልኮ በስተቀር በሌላ በምንም ነገር ሊከሱት እንዳልቻሉ እናነባለን። ዛሬ ብዙዎቻችን የሚያስከስሰን ነገር ቢኖር በግል እግዚአብሔርን አለማምለካችን

እንደሆነ እንጂ እንደ ዳንኤል አዘውትረን በማምለካችን አይደለም። የግል አምልኮው ግን ዳንኤልን ከአንበሶችም አፍ እንኳን እንደሚያድነው እርግጠኛ እንዲሆን ረዳው። ንጉሡ በማለዳ በመጣ ጊዜ የጠየቀው በግል ያመልከው የነበረው አምላክ በአደባባይ ጠበቃ ሆኖለት እንደሆነ ለማወቅ ነበር። «...ንጉሡም ተናገረ ዳንኤልንም፦ የሕያው አምላክ ባሪያ ዳንኤል ሆይ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶች ያድንህ ዘንድ ችሎአልን? አለው።» (ዳን. 6፡20) ይህ የአሕዛብ ንጉሥ ጥያቄ እጅግ አስደናቂ ነገር ነው። «ሁልጊዜ የምታመልከው» – የዳንኤል ሕይወት ይህ ዓይነት ነበር። ጥያቄው «ሁልጊዜ የምታገለግለው» የሚል አልነበረም። ሁልጊዜ ማምለክ መቻል ድንቅ ነገር ነው። ብዙዎቻችን ጌታ እንደ ዳንኤል ከአንበሳ አፍ እንዲያድነንና ለስሙ ምስክሮች እንዲያደርገን እንመኛለን። ያንን የሚያደርግ የግል አምልኮ እንዳይጎድለን ግን ሕይወታችንን መመርመር ይገባናል።

7. **ዕንባቆም፦** የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ «እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል።» (ዕን. 2፡20) ባለ ጊዜ ብቻውን ከአምላኩ ጋር እንደ ነበረ መገመት አስቸጋሪ አይሆንም።

8. **ጌታ ኢየሱስ፦** በሥጋ በምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ በግሉ ጠዋት ጠዋት ማልዶ ወደ ምድረ በዳ እየሄደ ይጸልይ እንደ ነበረና በሌላም ጊዜ ሙሉውን ሌሊት ከአባቱ ጋር በጸሎት ያሳልፍ እንደ ነበረ ቃሉ ይመሰክራል። «ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ።” (ማቴ. 14፡23)

“ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄደ በዚያ ጸለየ።» (ማር. 1፡35)

9. **ጴጥሮስ፦** ለአሕዛብ የነበረውን መለኮታዊ ራእይ ከእግዚአብሔር የተቀበለው በግል የጸሎት ጊዜው ነበር። “...ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ጣራው ወጣ። ተርቦም ሊበላ ወደደ፤ ሲያዘጋጁለት ሳሉም ተመስጦ መጣበት ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ...» (ሐዋ. 10፡10-11) ለጴጥሮስ ሰማያት ተከፈተው የታዩት በግል የአምልኮ ጊዜው ነበር።

10. **ዮሐንስ፦** ሐዋርያው ዮሐንስ ሰማያት ተከፍተው አስደናቂውንና ሊመጣ ያለውን ነገር በራእይ ያየው ብቻውን ፍጥሞ በምትባል ደሴት ላይ ሆኖ በጌታ ቀን (በዕለተ ሰንበት) በመንፈስ ሆኖ ሲያመልክ ነበር። ከዚያም በላይ ማንም ያላየውን የጌታ ኢየሱስን ውበትና ብርቱነት ከማየቱም በላይ በእርሱ እጅ ተዳሰሰ። ለአብያተ ክርስቲያናትም የሚሆነውን መልእክት ተቀበለ።

እንግዲህ እውነተኛ አምልኮ የሚጀምረው በግል የአምልኮ ጊዜ እንደሆነ አንዘንጋ። በግል የአምልኮ ጊዜ ነው እርሱን ወደ መምሰል የምንለወጠው፤ ለእርሱ የምንገዛው፤ ሰማያዊውን በረከት የምንቀበለው፤ የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማ የምናስተውለው፤ መልእክትንም የምንቀበለው። ከሁሉም በላይ ግን እንደሚገባን እርሱን የምናመልከው በግል የአምልኮአችን ጊዜ ነው። <u>እውነተኛና ፍሬያማ</u> አገልግሎት የግል አምልኮ ውጤት <u>ወይም ፍሬ ነው።</u>

የግል አምልኮ ሕይወትን ለማዳበር ራስን መግዛት ይጠይቃል። ሁልጊዜ ወይም ባላማቋረጥ እንድንጸልይ ቃሉ አጥብቆ ቢመክረንም፣ ይህ በግል ሕይወታችን እውን እንዲሆን የተለየ ጊዜ ደግሞ ወስነን በአምልኮ፣ በምስጋናና በጸሎት በፊቱ መቅረብ አስፈላጊ ነው። ጌታ ኢየሱስ ጠዋት ጠዋት በማለዳ ወደ ምድረ በዳ ይሄድ ነበር። ዳንኤል ጠዋት ቀንና ማታ በአምላኩ ፊት ጊዜ ለይቶ ይቀርብ ነበር።

እንዲሁም የግል የአምልኮ ጊዜያችን መንፈስ እንደመራን ከፈለግን የምንበረከክበት፣ የምንዘልበት፣ ድምጻችንን አንስተን ጌታ ባለማመደን ሁኔታ የምናመልክበት መንገድ ነው። ደስ እንዳለን እናመልከዋለን። ምክንያቱም በግል ከጌታ ጋር ያለን ጊዜ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ነው የግል የአምልኮ ጊዜ የምንለው። ከአባታችንና ከአዳኛችን ጋር ለብቻችንን የምንሆንበት ጊዜ ነው።

# ምዕራፍ 6

◊

## የቤተሰብ አምልኮ

ከግል አምልኮ ሕይወት ቀጥሎ በጣም አስፈላጊው አምልኮ የቤተሰብ አምልኮ ነው። በቤተሰብ አምልኮ ባል ለቤተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት ካህን መሆን ይኖርበታል። በብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት ተቀብለው ስለ ሕዝቡ መሥዋዕትን እያቀረቡ በእግዚአብሔር ፊት ከመቆምም ሌላ በእግዚአብሔር ፊት ሕዝቡን ይባርኩ ነበር።

«...ስትባርኩአቸው እንዲህ በሉአቸው:- እግዚአብሔር ይባርክህ፤ ይጠብቅህም እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፥ ይራራልህም እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ።» (ዘኁ. 6፡23-26)

ለዚሁ ዓይነት አገልግሎት በአዲስ ኪዳን ሁላችንም ካህናት ተብለን ተጠርተናል።

«ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፣ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።» (ራእይ 1፡6)

«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁ የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ።» (1ኛ ጴጥ. 2፡9)

ለዚህ የክህነት አገልግሎት የቤተሰብ ራስ በመሆን ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ ቤተሰቡን ወደ እውነተኛ መንፈሳዊ አምልኮ መምራት ያለበት ባል መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ይህም ማለት ሚስት ወይም ልጆች አስተዋጽኦ የላቸውም ወይም በመንፈሳዊ ሕይወት ዝቅ ያሉ ናቸው ማለት አይደለም። ቀድሞ ኃላፊነት ለባል ስለ ተሰጠ ምሳሌ በመሆን መቅደም አለበት ማለት ነው።

ኢዮብ ለዚህ መልካም ምሳሌነት ነበረው። ቤተሰቡን እንደ ካህን ሆኖ ያገለግላቸው እንደነበር ቃሉ ሲመሰክርለት፦ «የግብዣውም ቀኖች ባለፉ ጊዜ ኢዮብ– ምናልባት ልጆቼ በድለው እግዚአብሔርንም በልባቸው ሰድበው ይሆናል ብሎ ይልክና ይቀድሳቸው ነበር። ኢዮብም ማልዶ ተነሣ እንደ ቍጥራቸውም ሁሉ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። እንዲሁ ኢዮብ ሁልጊዜ ያደርግ ነበር።» (ኢዮብ 1፥5) ይላል። ለቤተሰብ አምልኮ ከዚህ ጥቅስ የምንረዳቸው ቁልፍ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

1. «ይልክና ይቀድሳቸው ነበር» – የቤተሰብ ሕይወት በቅድስና እንዲጠበቅ ጥንቃቄ ማድረግ ለቤተሰብ አምልኮ መሠረታዊ ነገር ነው። ይህ ካልሆነ እንደ ያዕቆብ ቤተሰብ የጣዖት አምልኮ በቤት ውስጥ ይጀምራል። "ያዕቆብም ለቤተሰቡና ከእርሱ ጋር ላሉት ሁሉ እንዲህ አለ፦ እንግዶቹን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ፣ ንጹሐንም ሁኑ፣ ልብሳችሁንም ለውጡ ተነሥተንም ወደ ቤቴል እንውጣ፤" (ዘፍ. 35፥2)

2. «እግዚአብሔርን በልባቸው...» – የቤተሰብ አምልኮ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው የልብ ንጽህናና የመንፈስ አንድነት ሲኖር ነው። ባልና ሚስት አንድነታቸውን ካልጠበቁ ጸሎታቸው ስለማይሰማ እንደው የልማድ ድርጊት እንጂ እውነተኛ አምልኮ ለማካሄድ አይችሉም። ቃሉም «..ከሚስቶቻችሁ ጋር

በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፣ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል..» ይለናል። (1ጴጥ. 3፡7) ከዚህ ጋር በግልጽ ለሚታየው ብቻ ሳይሆን ለልብ ቅድስና መጠንቀቅ አለባቸው። አምልኮ እግዚአብሔርን ከሚወድና ከሚፈራ ልብ የሚመነጭ ውዳሴ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ይህም ማለት በቅርቡ መተዋወቅና መተራረም አስፈላጊ ነው ማለት ነው።

3. «ኢዮብ ማልዶ ተነሣ...» – የቤተሰብ አምልኮ ቤተሰቡ እግዚአብሔርን በማወቅ የሚያድግበትና እግዚአብሔርን የሚያከብርበት እንዲሆን፦ አንደኛ/ ወላጆች ስለ ቤተሰቦቻቸው በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆም አለባቸው። ሁለተኛ/ ይህ ልማድ በየዕለቱ የሚከናወን ነገር መሆን አለበት። ይህ ማለት አባት በየቀኑ ቤተሰቡን (ሚስቱና ልጆቹ) በጌታ ፊት የማቅረብ ኣላፊነት አለበት። እናትም ደግሞ እንዲሁ። አብረው በአንድነት ደግሞ ለቤተሰባቸው የመጸለይ፣ የማስተማርና ምሳሌ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው። ቃሉም "እኔም ዛሬ አንተን የማዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፣ በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም፣ ስትነሣም ተጫወተው።" (ዘዳ. 6:6-7)

4. «እንደ ቁጥራቸው ሁሉ...» – ይህ የሚያሳስበን ለልጆቻችን ወይም ለቤተሰባችን በግል በስማቸው መጸለይ እንዳለብን ነው። እግዚአብሔር ለልጆቻችን የግል ጥሪ፣ ጸጋና ምሪት ስላለው ያንን በመረዳት ለእነርሱ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብና ለእግዚአብሔር የሚያመቹ ሆነው እንዲያድጉ የመቃተት ሃላፊነቱ የቤተሰብ ነው።

5. «እንዲሁ ኢዮብ ሁልጊዜ ያደርግ ነበር።» – የቤተሰብ የአምልኮ መሠዊያ የማይፈርስ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር ደግሞ መሥዋዕቱ ሁልጊዜ ትኩስ መሆን አለበት።

6. የቤተሰብ አምልኮ "የውሳኔ ጉዳይ ነው" – ኢዮብ ካህን ስለሆነ ሁልጊዜ ይህንን የአምልኮ ሥርዓት ያደርግ ነበር። ሌላው ይህንን ዓይነት ውሳኔ ያስተላለፈው ሰው ኢያሱ ነው። ስለ ቤተሰብ አምልኮ ስናስብ ኢያሱ በእስራኤል ጉባኤ ፊት ያስተላለፈውን ቆራጥና የማያወላውል ውሳኔ ማስታወስ ያስፈልጋል። «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።» (ኢያሱ 24፥15) ኢያሱ የጀመረው በራሱ ነው። «እኔና» – የቤተሰብ አምልኮ ቀደም ሲል እንደ ጠቀስኩት የሚጀምረው በቤተሰብ ራስ ነው። የእርሱ ውሳኔ ለቤተሰቡ የአምልኮ ሕይወት መሠረት ይጥላል። ከኢያሱ ሕይወት በጣም የሚባርከው ውሳኔ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የእርሱ ውሳኔ የቤተሰቡም ውሳኔ መሆኑን ሳያወላውል ማሳወቁ ነው። ኢያሱ ከሁለት ሚሊዮን ያላነሱትን ሰዎች የመምራት፣ ሰባት ኃሳዎችን ተዋግቶ አገር አስለቅቆ እስራኤላውያንን የተስፋ ምድር የማውረስ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ነበር። ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ሥራና አገልግሎት ስለሚበዛብኝ ከቤተሰቤ ጋር ለቤት አምልኮ ጊዜ የለኝም አላለም። ነገር ግን የቤተሰቡን መንፈሳዊ ሕይወት በጣም ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። የዛሬ አገልጋዮች የኢያሱን ቃል አርአያነት የምንከተል መሆን አለብን። ሁልጊዜ ማስተዋል የሚገባን ነገር ቢኖር ፍሬያማና ዘለቄታ ያለው አገልግሎት የሚጀምረው በግል አምልኮና በቤተሰብ አገልግሎት መሆኑን ነው። የራሴን ቤተሰብ ማገልገል ካልቻልኩ ሌሎችን እንዴት ማገልገል እችላለሁ። ቃሉም «ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?»

የሚለው ለዚህ ነው። (1ጢሞ. 3፡5) አገልግሎት የሚጀምረው ለቤተሰባችን ካህን በመሆን ነው።

«የቤተሰብ አምልኮ እንዴት መሆን አለበት?» ለሚለው ጥያቄ ሁለት ዓይነት የቤተሰብ አምልኮ ቢኖር መልካም ነው።

አንደኛው/ ሁሉንም ቤተሰብ የሚጨምር የአምልኮ ጊዜ ያስፈልገናል። ይህ እንደ ቤተሰብ ሁኔታ ጠዋት ወይም ማታ ሊሆን ይችላል። ይህ የቤተሰብ የአምልኮ ጊዜ ቤተሰብ ከጌታ ቃል አንብበው በአንድነት ምስጋናቸውን፤ ጥያቄያቸውንና ውዳሴያቸውን ይዘው ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡበት ሰዓት ነው። ይህ ቤተሰብን ሁሉ የሚመለከት ስለሆነ ሁሉም እንዲካፈሉበት ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ነው። የውይይቱ ጥልቀትና የጸሎቱ ጊዜ በተሳታፊዎቹ (በልጆቹ) ዕድሜ የሚወሰን ነው። የልጆቹንም ፍላጎትና ስሜት መጠበቁና፣ አስተያየታቸውንም ማክበሩም አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛው/ የባልና የሚስት የተለየ የአምልኮ ጊዜ መኖሩ መልካምና አስፈላጊ ነው። ጊዜውንና ርዝመቱን እነርሱ የሚወስኑት ነገር ነው። ይሁን እንጂ ከቤተሰብ የሚደብቁት ነገር አለ ለማለት ሳይሆን ሁለቱ ብቻቸውን ሆነው በአንድነት ለእግዚአብሔር ለአምላካቸው መልካም መዓዛ ያለውን የአምልኮ መሥዋዕት ማቅረብ መቻል አለባቸው። እንግዲህ በዚህ መሠረት በቤተሰብ ውስጥ የሚቀርቡ ሦስት የተለያዩ የአምልኮ መሥዋዕቶች አሉ ማለት ነው።

- የግል የአምልኮ ጊዜ – በቤተሰብ ውስጥ ጌታን በግል የሚያውቁና የሚወዱ የግል የጥሞና ጊዜ ያስፈልጋቸዋል።

- የባልና የሚስት የአምልኮ ጊዜ – ባልና ሚስት በአንድ ልብ ሆነው በስምምነት ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው የአምልኮ መሥዋዕትን ማቅረብ ይገባቸዋል።

- የቤተሰብ የአምልኮ ጊዜ – «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።» ለማለት የሚያስችል ሁሉንም የሚጨምር የውዳሴ ሰዓት ነው።

እነዚህ በቤት የሚካሄዱ አምልኮዎች በእውነትና በመንፈስ ከሆኑ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ቤት የአምልኮ ቤት ይሆናል ማለት ነው። የእያንዳንዱ ቤት የአምልኮ ችቦ በቤተ ክርስቲያን አንድ ላይ በሚመጣበት ጊዜ የአምልኮው እሳት ከፍ ብሎ ይበራል። ይህም ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ የቤት አምልኮ ውጤት ወይም ፍሬ ይሆናል።

የቤተሰብን አምልኮ እንደ ግል አምልኮ ማድረግ አንችልም። ወደ ቤተሰብ አምልኮ በምንመጣበት ጊዜ ሌሎች ደግሞ ከሌላ ልምምድ የሚመጡ አሉ። ስለዚህ የእነዚያንም መንፈስ መጠበቅ አለብን። ወደዚህ አምልኮ ስንመጣ ሁልጊዜ ለሌላ አካል መጠንቀቅ አለብን። እኔ መጮህ የምወድ ከሆነ ዝግ ማለት ይኖርብኝ ይሆናል። የቤተሰብ አምልኮ የቤተሰብን አንድነት የሚያጠነክር መሆን ይገባዋል። አለበለዚያ ግን ሌላውን አካል በመረበሽ እግዚአብሔርን በበለጠ እንዳያመለክ እንቅፋት ይሆናል። እኔና ባለቤቴ ስናመልክ መጀመሪያ በውስጡ የሚመጣው ነገር መዝሙር ነው። ምክንያቱም ብቻዬን ሳመልክ መዘመር ስለማልችል መዘመር በጣም ይናፍቀኛል። ስለዚህ ከባለቤቴ ጋር የግል ጊዜያችን ስናደርግ ብንዘምር ደስ ይለኛል። ምክንያቱም ያ ጉድለቴ የሚሟላልኝ ከእርሷ ጋር ስናመልክ ነው። እግዚአብሔር

እርሷን የሰጠኝ እንዲሁም ለዚህ ነው። ይህ ማለት የቤተሰብ አምልኮ የሌላውን ጉድለት በመሙላት አብሮ በጸጋ ማደግ ማለት ነው።

# ምዕራፍ 7

◊

## የቤተ ክርስቲያን አምልኮ

የቤተ ክርስቲያን አምልኮ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መገለጥ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር በሚመጡት ዘመናት ከግለሰብና ከቤተ ክርስቲያን የሚፈልገው እውነተኛ የሆነውን አምልኮ ነው። በተለይም በቤተ ክርስቲያን አምልኮን የሚመሩ ሰዎችና እንዲሁም መዘምራን በጣም ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ሊያደርገው ላለው ነገር ጉባኤውንና መንፈሱን የሚያዘጋጁት የአምልኮ መሪዎችና መዘምራን ናቸው። ይህ አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትን ሰዎች ለሰልፍ የሚያዘጋጅ አገልግሎት ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ነው። በአንድነት እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክን ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው የሕዝቡ አምልኮ ለእግዚአብሔር ልብ በጣም የቀረበ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን ወይም በጸሎት ቤት በአንድነት ሲሰበሰብ ትኩረቱ አምላኩን በአንድነት ለማምለክ መሆን አለበት። አምልኮው ቦታውን ከያዘ ሌላው ሁሉ በቀላሉ ይስተካከላል።

የእሁድ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ በዝማሬ፤ በውዳሴ፤ በጸሎት፣ በቃሉ ንባብና ገለጻ ላይ የተመሠረተ ነውና በአንድነት ለምናቀርበው የአምልኮ ጊዜ መዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው።

## ለቤተ ክርስቲያን አምልኮ የግለሰብ ዝግጅት

እግዚአብሔርን በአንድነት በማምለክ ለምናሳልፈው ጊዜ ዝግጅቱ፡ በቤታችን መጀመር ይኖርበታል። «እንዴት ነው የምንዘጋጀው?» ለሚለው ጥያቄ፦

**1. የግልና የቤተሰብ የአምልኮ እሳት እንዳይቀዘቅዝ መጠበቅ።** የአምልኮ እሳት ሲደክም የግል ሆነ የአንድነት አምልኮ ኃይሉን ስለሚያጣ ለታይታ የሚደረግ ውጫዊ ሥርዓት ብቻ ይሆናል። ለዚህ ነው ቃሉም "የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል" (2ጢሞ. 3:5) የሚለው።

**2. የልብ ዝግጅት ማድረግ።** በማንም ሰው ላይ ቅሬታን ይዘን እንዳንመጣ ልባችንን መመርመር አለብን። ቃሉም፦ «መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።» ይላልና። (ማቴ. 5፡23-24) አብዛኛውን ጊዜ ራሳችንን እንድንመረምር የምንጠየቀውና ይህን እርምጃ የምንወስደው የጌታን እራት ከመውሰዳችን በፊት ነው። ይህም መልካም ነገር ነው። ነገር ግን ይህ ራስን የመመርመሩ ጉዳይ ሁልጊዜ የምንለማመደው ነገር መሆን አለበት። ምክንያቱም ኃጢአት በተለይም ይቅርታን አለማድረግ ወይም ቂምን መያዝ ለአምልኮ ታላቅ እንቅፋት እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ጉዳይ ነው።

3. **የጊዜ ዝግጅት ማድረግ።** በተለይም ለእሁድ አምልኮ ከጊዜው አንጻር መዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ዝግጅት የሚከተለውን ይጨምራል።

- ቅዳሜ ማታ በጊዜ በመተኛት። ቅዳሜ ሌሊት በቂ ዕረፍት ካላገኘን እሁድ ጠዋት በጊዜ ተነሥተን በነቃ ሰውነት እግዚአብሔርን ማምለክ አንችልም። የማይቻል ካልሆነ በስተቀር ቅዳሜ ማታ ያለማምሸት ይመረጣል። ልጆችን በጊዜ ማስተኛት ለዝግጅቱ በጣም ይረዳል። ሥጋችን ሲደክም ማምለክ ያስቸግራል። እሁድ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቁጭ ብሎ ማንቀላፋት፣ ለታላቁ እግዚአብሔር የሚገባውን አለመስጠት ከመሆኑም በላይ በሰውም ዘንድ ትዝብትን ያመጣል። አምልኳችንም ልማድ ብቻ ይሆናል።
- ለእሁድ ጠዋት የሚያስፈልገውን ቅዳሜ ማታ ማሰናዳት። ለምሳሌ ያህል፦ የልጆችን ልብስ ማዘጋጀት፤ ቁርስ የሚበሉ ከሆነ ቅዳሜ ማታ አስፈላጊ ነገሮችን ማጠናቀቅ። የቅዳሜ ዝግጅት የእሁድ ጠዋት የሃሳብ ግጭትን ያስወግዳል። ይህ ካልሆነ ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ስለሚዘገዩ ባልና ሚስት በቀላሉ ለግጭት ይጋለጣሉ። እርሱ "ለምን አዘገየሽኝ?" ይላታል- እርሷ ደግሞ "አንተ ብትረዳኝ ኖሮ አይረፍድብንም ነበር" ትላለች። እንደዚህ እያሉ ቤተ ክርስቲያን ይደርሳሉ። እዚያ ሲደርሱ መዝሙር እየተዘመረ ስለሆነ መንፈሳቸውም ሆነ ልባቸው ሳይዘጋጅ ከሌሎች ጋር የቀረውን ዘምረው መልእክት ሰምተው ይመለሳሉ። ይህ ሥርዓትን መፈጸም እንጂ አምልኮ አይደለም።

4. **የመንፈስ ዝግጅት** - ጌታን ለማምለክ የመንፈስና የአዕምሮን ዝግጅት ይጠይቃል። ለአምልኮ መንፈስን ማዘጋጀት

ከልማድ ሕይወት ነፃ ያወጣል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የመንፈስ አምልኮ ስለሆነ እርሱ የሚፈልገው በመንፈስና በእውነት የሚያመልኩትን ነው። የመንፈስ ዝግጅት ከሌለ በእውነት ማምለክ አይቻልም። መዝሙረኛው «ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅማለች» (መዝ. 84፡2) ያለው የመንፈሱን ጉጉትና መዘጋጀት ሲገልጽ ነው። እግዚአብሔርን ለመገናኘትና ለማምለክ መናፈቅ ያስፈልገናል።

**5. የእግር ዝግጅት** - ይህ ፈቃዱን ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በጥንቃቄ መግባትና መውጣት ያስፈልጋል። "ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ፤ ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መሥዋእት ይበልጣልና፤" (መክ. 5:1) ስለሚል ወደ እግዚአብሔር ቤት ስንገባ በአክብሮትና በፈሪሃ እግዚአብሔር መሆን አለበት።

ጸሎት ቤትን ልዩ የሚያደርገው የእግዚአብሔር እዚያ መገኘት ነው። «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።» (ማቴ. 18፡20) በሚለው ቃል መሠረት እግዚአብሔር ያለበት ቦታ ሁሉ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔርም «ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።» (ዘፀ. 3፡5) ሙሴ ብዙ ዓመታት በዚያ ምድረ በዳ ተመላልሶ ነበር። ያ ሥፍራ ከሌላው ሁሉ ምንም ልዩነት አልነበረውም። በዚያ ቀን ግን ቅዱስ የተባለው የእግዚአብሔር ሕልውና በዚያ ስለ ተገለጠ ሙሴ ጫማውን ማውለቅ ነበረበት። ከቤተ ክርስቲያን በጣም ጎድሎ የሚታይ ነገር ቢኖር በቅዱስ ፍርሃት መመላለስ ነው። መድረኩም በቅድስና መያዝ አለበት። ሁለንተናችንን ለአምልኮ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይ አገልጋዮች

መድረኩን ከመለማመዳችን የተነሣ እንዳንደፍር መጠንቀቅ ይኖርብናል።

6. **የእጅ ዝግጅት ያስፈልጋል።** የእጅ ዝግጅት የሕይወት ንጽህናና መስጠትን እንዲሁም ለእግዚአብሔር መማረክን ያመለክታል። ከዚህ ጋር እግዚአብሔር በእጃችን ውስጥ ያስቀመጠውን ይዘን መቅረብ ተገቢ ነው። "በፊቱም አንድ ሰው ባዶ እጁን አይታይ።" (ዘጸ. 34:20) ይህ ማለት ገንዘብ ከሌለን ወደ እግዚአብሔር ቤት አንሂድ ማለት አይደለም። ነገር ግን አንደኛ እግዚአብሔር ባርኮን እያለ ከስስት ወይም ከቸልተኝነት የተነሣ ባዶ እጅ መቅረብ አይገባም ማለት ነው። ሁለተኛ ከሌለን ለዘሪ ዘርን የሚሰጥ እርሱ ነውና በእምነት እንጠይቀው ለማለት ነው። ሦስተኛ ገንዘብም በእጃችን ባይኖር የከንፈሮቻችንን ፍሬ ምስጋናን ይዘን እንቅረብ ማለት ነው።

# ም ዕ ራ ፍ 8

◊

## የአምልኮ መሪዎች ዝግጅት

አምልኮ በጣም ታላቅና የከበረ ነገር ስለሆነ

- የሙዚቃ መሣሪያ የሚጫወቱ፤
- መዘምራን፤
- የአምልኮ መሪው፤
- አስተናጋጆች እና
- መድረኩን የሚረግጡ ሁሉ፤ መንፈሳቸውንና ልባቸውን በጸሎት አዘጋጅተው መምጣት አለባቸው።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገቡም በኋላ ከሁሉ በላይ የከበረ አምላክ፤ የጌቶች ሁሉ ጌታና የነገሥታት ንጉሥ እዚያ መኖሩን በማስተዋል፤ በአክብሮት፤ በፍርሃት በአምልኮና በምስጋና መንፈስ መመላለስ ይጠበቅባቸዋል።

ወደ መድረክ የሚወጡ ሰዎችም የሚያደርጉትን ሁሉ በአክብሮትና በአግባብ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ደግሞ በመዝሙር አምልኮን የሚመሩ ሰዎች የክህነት ልብሳቸውን ለብሰው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመምራት እንደ ቆሙ መገንዘባቸው ከብዙ ስህተት ይጠብቃቸዋል። "እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ:- ልጅ አባቱን:- ባሪያም ጌታውን ያከብራል፤ እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ ወዴት አለ? ይላል የሠራዊት ጌታ

እግዚአብሔር።" (ሚልክ. 1:6) ይህ መሪ ሃሳብ አገልጋይ ሁሉ በግልም ሆነ በጉባኤ ለአምላኩ መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የመገናኛ ድንኳን የሚባለው የደጁ አደባባይ አለ። የውስጡ ቅድስተ ቅዱሳን አለ። ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ለመግባት ከቅድስተ ቅዱሳኑ በፊት ያለው የዕጣን መሠዊያ ነው። የዕጣን መሠዊያው አምልኮ፣ የምስጋናና ዝማሬ ምሳሌነት ያለው ነው። ስለዚህ ከዕጣኑ መሠዊያ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀው ሙላት ከመግባታችን በፊት አምልኮአችንና መንፈሳችን አንድ ሆኖ እግዚአብሔርን ማምለክ አለብን። አንዳንድ ጊዜ ተለያይተን እናመልካለን። አዕምሮ እግዚአብሔርን ያመልካል መንፈስ ግን አያመልክም። መንፈስ ያመልካል አዕምሮ አያመልክም። ነገር ግን ሁሉ በአንድነት ተጣምሮ በዚያ በዕጣኑ መሠዊያ ላይ መሆን አለበት። በዚያ በዕጣኑ መሠዊያ ላይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ሆኖ ሁለንተናችን ከቀረበ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ቅድሰተ ቅዱሳኑ ውስጥ ያስገባናል። ይህ ማለት አምልኮ ወደ እግዚአብሔር በጣም የቀረበ ጉዳይ ነው ማለት ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ከመመለሱ በፊት ቤተ ክርስቲያን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ትገባለች (በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ተዘጋጀላት ሙላት)። የእግዚአብሔርንም ክብር በሙላት ታያለች። ያንን ለማድረግ በመስቀሉ አማካይነት ወደ መሠዊያው መጥተን አገልግሎታችንን ሁሉ እንሰብስብ። በቀኝ በኩል ገበታ አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መብራት አለ፤ እነዚህን ሁሉ በአንድነት አምጥተን በዕጣኑ መሠዊያ ላይ እናስቀምጥ። ያን ጊዜ አገልግሎታችን፣ ስጦታችን፣ ዝማሬያችን፣ ኑሮአችን፣ መውጣት መግባታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሆንና እግዚአብሔር ቅድስተ ቅዱሳኑን ይከፍታል። እግዚአብሔር ወደ

እዚያ ሆነን እናገለግላለን። እግዚአብሔር የዕጣን መሠዊያውን በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ያስቀመጠበት ምክንያት ሥጋ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ስለማይገባ ነው። ያልተሠዋ የቀረ ነገር ካለ እዚያ መሞት አለበት። በአምልኮ፤ በምስጋና ውስጥ መሞት አለበት። ከዚያም እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀልን ወደ እግዚአብሔር ሙላት በአምልኮ እንገባለን።

የመዘምራን አገልግሎት ቆሞ መዘመር ብቻ አይደለም። ሕዝቡን በዝማሬ መምራት መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ወደ አገልግሎት በሚመጡበት ጊዜ ዘወትር ተዘጋጅተው መምጣት አለባቸው። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወይም ጉባኤውን አቅጣጫ እንዲይዝ መምራትና ወደ ታላቅ አምልኮ የማስገባት ሃላፊነት አለባቸው።

የሚከተሉት ሃሳቦች ለአምልኮ መሪዎች ይረዳሉ ተብለው የቀረቡ ናቸው። ከነዚህ ሃሳቦች በላይ ግን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

1. መዝሙር በመምራትና በስብከት መካከል ያለውን ልዩነት ማስተዋል። የአምልኮ መሪ ኃላፊነት ስብከት መስጠት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አምላኩን በእውነትና በመንፈስ ሆኖ እንዲያመልክ መርዳት ነው። መሪዎች የሚሰጡት አስተያየት ወይም የቃሉ ገለጻ ትክክል ስላልሆነ ሳይሆን ለሁሉም ጊዜና ቦታ ስላለው እንዲሁም እንደ ስጦታቸው መሰለፋቸው የሚበልጥ ፍሬ ስለሚያመጣ ነው። በአምልኮ ጊዜ የሚፈስ ቅባት አለ። በመልእክት ጊዜ ለቃሉ ገለጻ የሚሰጥ ቅባት አለ። ስለዚህ በአምልኮ ጊዜ የሚያስፈልገው ስብከት ሳይሆን ዝማሬና ውዳሴ ነው። ቃሉን ማንበብ አስፈላጊ ከሆነ ዝማሬ ከመጀመሩ በፊት ማንበቡ መልካም ነው። አምልኮ የመምራትን ፈተና ማለፍ ይኖርብናል። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት ስንቆም ፈተናው፣

በሃሳባችን የመጣው ሁሉ ለጉባኤው በጣም የሚያስፈልግ ስለሚመስለን ያንን የማስተላለፍ ግዴታ ያለብን ይመስለናል። ሃላፊነታችን ግን ሕዝቡን በአምልኮ አነቃቅተን ጊዜውን ሳናባክን ለሰባኪውና ለመንፈስ ቅዱስ መድረኩን ማዘጋጀት ብቻ ነው።

**2. ለመንፈስ ቅዱስ ምሪትና አሠራር መታዘዝ።** አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በጥቂት መዝሙሮች ብዙ ነገር ይሠራል። መሪ የዚህን ዓይነት አሠራር ካላስተዋለ ከመዝሙር ወደ መዝሙር በመዝለል ጊዜ ሊያባክን ይችላል። ሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሌላ መዝሙር ወይም አዝማቾች ሕዝቡ እንዲያልፍ እየፈለገ መሪው ዝማሬው ብቻ ስለ ተስማማው እዚያው የሚቆይበት ጊዜ አለ። በጸሎት ተዘጋጅቶ የመንፈስ ቅዱስን አሠራር ከመከተል በስተቀር ለዚህ ምንም ሕግ የለም። ለመንፈስ ቅዱስ መመሪያን ማውጣት አይቻልም። አሠራሩን ለይቶ ግን በትህትና መከተል ይቻላል። «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁን ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ከመንፈስ የተወለደ እንዲሁ ነው።» (ዮሐ. 3፥8) «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።» (ሮሜ 8፥14)

**3. የዝማሬን ቅደም ተከተል መለየት።** አንዳንዱ መዝሙር የንስሐ፤ ሌላው የምስጋና፤ ሌላው የደስታ፤ ሌላው የውዳሴ ወዘተ ነው። አንዳንዱ በፍጥነት ይዘመራል ሌላው በቀስታ፤ አንዳንዱ ወደ ጸሎት ይመራል ሌላው ወደ አድናቆት። በዚህ ወቅት አንዳንዱ በዝምታ ወደ ማምለክ ይወስዳል፤ ሌላው ወደ መዝለል፤ ሌላው ደግሞ ወደ ማጨብጨብና ወደ ማሸብሸብ፤ ሐሴት ወደ ማድረግ ይመራል። ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እስከሆነ ድረስ በጣም ውብ ነው። ከእርሱ የተሰጠ ሁሉ

አገልግሎት አለው። አምልኮ የሚመራ ሰው በመጠኑም ቢሆን እነዚህን መለየት ይኖርበታል። የምስጋና ሲያዘምር ቆይቶ የንስሐና የለቅሶ ከዚያ ደግሞ የአምልኮ፤ የውዳሴን እያለ ከአንዱ ወደ ሌላው በአንዴ መዝለል መንፈስን ይረብሻል። ይህ እንዳይሆን አስቀድሞ መዘጋጀቱ ይረዳል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ መሄድን መማር አለብን። መዝሙራችን መያያዝ አለበት። ዝም ብለን ወደ እግዚአብሔር ደጅ መግባት፤ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከገባን በኋላ ምንም ቃል አያስፈልግም። «መንፈስ የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ» ስለሚል መንፈስ ቅዱስ ሊሠራ ያለውን ይሥራ። ስለዚህ በአምልኮ ወቅት፣ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከአንድ ዝማሬ ወደ ሌላው ከአንዱ ሙዚቃ ወደ ሌላው መሸጋገር እጅግ መልካም ነው። ሌላ ጊዜ ደግሞ ውለታውን አስቦ በፊቱ ዳዊት የእግዚአብሔር ታቦት በተመለሰ ጊዜ እንዳደረገው ሐሴት ማድረግም አለ። እግዚአብሔር ሊሠራ ላለው የሰውን ልብ ያዘጋጃል።

በተለይ ለእሁድ አምልኮ መልካም የሚመስለንን ትንሽ ብንጠቁም። (ይህ የግል ምክር ወይም አስተያየት እንጂ ሁሉም እንደዚህ ያድርግ ወይም ካላደረገ ትክክል አይደለም ለማለት አይደለም።)

- አምልኮን ሙዚቃው ፈጠን ባለ የምስጋና መዝሙር ማስጀመሩ ይመረጣል። እሁድ ጠዋት ሰዎች ከተለያየ ሁኔታ ስለሚመጡ ይህ አሳባቸውን ለመሰብሰብ ይረዳቸዋል። ጉሮሮአቸውም ስለሚከፈት ድምጻቸው በቀላሉ መውጣት ይጀምራል።

- የመጀመሪያዎቹ ጥቂት መዝሙሮች ወይም አዘማቾች ብዙ ምዕመን የሚያውቃቸው ቢሆኑ ሰዎች በቀላሉ ሃሳባቸውን

በመሰብሰብ ታዛቢ ከመሆን ይልቅ ተካፋዮች የመሆን ዕድል ይኖራቸዋል።

- በምስጋና መዝሙሮች መቀጠል። ምስጋና ውስታውን እንድንቆጥር ስለሚያደርገን ከዚያ በኋላ ስለ ታላቅነቱ፤ ስለ ክብሩ፤ ስለ ግርማው፤ ስለ ችሎታውና ወዘተ. መዘመር ላይከብድ ይችላል።

- በውዳሴ መዝሙሮች መቀጠል። ከምስጋና በኋላ በዝግታ ሙዚቃ ረጋ ባለ መንፈስና በማስተዋል እንደ ሰብአ ሰገል የስጦታ ሳጥኖቻችንን ከፍተን በአክብሮት ውድ የሆነውን ከነፍሳችን የመነጨ ውዳሴንና አምልኮን ወዘተ. በእግሩ ሥር ማስቀመጥ ወደሚያስችለን ሁኔታ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህ ውበቱን እንድናይ፣ ግርማውንና ቅድስናውን እንድናስተውል ይረዳናል።

- በጸጥታ የአምልኮ መንፈስ መጨረስ። ከዝማሬና ከአምልኮ በኋላ ለዝምታ ጊዜን መስጠት መልካም ነው። በንጉሡ ፊት ከቀረብን ንጉሡ የሚለው ነገር ካለ ክብሩንና፤ ታላቅነቱን እያሰብን ለትንሽም ጊዜ ቢሆን ጸጥ ማለቱ በጣም መልካም ነው። ልዩ መልእክት የተሰጠው ሰው ካልሆነ በስተቀር በዚህን ጊዜ ማንም ድምጹን ከፍ በማድረግ ሌሎችን ባይረብሽ በጣም መልካም ነው። "ሰባተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።" (ራእይ 8:1) ይህ እግዚአብሔር ስለ አቀረብንለት መሥዋዕት የሚናገርበት ጊዜ ነው። ካልሆነም በጸጥታ በቃሉ በኩል ሊናገር ላለው ነገር ነፍስንና ልብን ያዘጋጃል።

4. የአምልኮን ትኩረት ማወቅ። የአምልኮ ትኩረት አምላኪው ላይ ሳይሆን የሚመለከው ታላቁ አምላክ ላይ መሆን ይኖርበታል። የአምልኮ ትኩረት እግዚአብሔር ላይ ከሆነ ሰዎች በውጫዊ ታይታ ላይ ጊዜ አያጠፉም። ትኩረቱ እግዚአብሔር ከሆነ አምልኮ የፍቅር መግለጫ ነውና ሰዎች እጃቸውን አንሥተው ያወድሱታል፤ እያጨበጨቡ ያከብሩታል፤ እያሸበሸቡ ያመሰግኑታል፤ በዝምታ ያደንቁታል። የአምልኮ ቁምነገሩ እርሱን አይቶ እርሱን በሙሉ ልብና ሁለንተና የሚገባውን መሥዋዕት ማቅረብ ነው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ጌታን ስለ አየ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ. 1፥36) ሲል መሰከረ።
- እንዲሁም «... እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ።» (ዮሐ. 7፥56)
- «...ሰባት የወርቅ መቅረዞች አየሁ፥ በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ» (ራዕይ 1፥12-13)
- "ከዚያም በኋላ አየሁ፡- እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፣ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምጽ፡-- ወደ እዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።" (ራእይ 4:1)
- «በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።» (ራዕይ 5፥6)
- «...እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር።» (ኢሳ.

6፡1) የአምልኮአችን ትኩረት ጌታ ኢየሱስን በአዳኝነቱ፣ በአማላጅነቱና በግርማ ሞገሱ ማየት መሆን አለበት።

**5. የአምልኮን መሠረት መረዳት።** የአምልኮ መሠረት የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ያለ እግዚአብሔር ጸጋ እርሱን ማምለክ የሚችል ፍጥረት የለም። ጸጋው ፍቅሩን ተረድተን እንድንቀበል ያደርገናል። እውነተኛ አምልኮ ፍቅሩን ከተረዳ ልብ የሚመነጭ ውዳሴ ነው።

**6. የእግዚአብሔርን ሕዝብ እግዚአብሔር ሊያደርገው ላለው ነገር በአምልኮ ማዘጋጀት።** ስለዚህ የመሪዎች መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትና በመንፈስ ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ በጣም አስፈላጊ ነው።

**7. የግል ልምምድን እንደ ቋሚ ደንብ ቃል አለማቅረብ።** ጌታን በምናመልክበት ጊዜ የግል ልምምዳችንን ይዘን በመምጣት ሁሉም እንደ እኔ ያምልክ ማለት ለአንድነት አምልኮ አይረዳም። እግዚአብሔር ሆይ በአካሌ በኩል ልታደርገው ያልከውን ነገር ራሴን በመስጠት እኔም እንደ ብልት ድርሻዬን አበረክታለሁ ማለትን መቻል አስፈላጊ ነው። ብዙ ጊዜ ለአካል የማይመች የግል ልምምድ ለመንፈስ ሥራ እንቅፋት ይሆናል።

ለምሳሌ ያህል-- አንዳንድ ጊዜ ልክ አምልኮ ተጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን መሥራት ሲጀምር የክርስቶስ አካል ሥራ ምን እንደሆነ የማይረዱ መጮኽ ወይም ለየት ያለ ነገር ማድረግ ይጀምራሉ። እንደዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን አካል ሥራና የጌታን አሠራር በአካል አንድነት ውስጥ መረዳት ይኖርባቸዋል። አካል ሲገጣጠም አንዱ ለሌላው መታዘዝና ከሌላው

ጋር መስማማት አለበት። መዋሃድ የሚባለውን ነገር በሥራ ላይ ማዋል ማወቅ አለበት። በተለይም በአምልኮ አካል ስንል ሁሉም በአንድ ላይ በአንድ መንፈስ መሄድ ማለት ነው። እስቲ አንዴ ጸዋ በሉ ሲባል ለብቻ መጮኽ አይገባም። በግል የተለማመደው ይህን ስለሆነ ሁልጊዜ መጮህ ያለበት የሚመስለው ሰው አለ። ለእርሱ ስሜቱን መግለጹ ይሆናል የአካል የማምለክ መንፈስን ግን ይረበሻል።

ሌላው ደግሞ ሲዘመር በልሳን ጮክ ብሎ ይናገራል፣ በመሠረቱ በልሳን መናገር ትክክል አይደለም ለማለት አይደለም ነገር ግን ለሁሉም ጊዜ፣ አግባብና አሠራር ስላለው በማስተዋል ነገሮችን ማድረግ ለጉባኤ አምልኮ አስፈላጊ ነው ለማለት ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ መሄድና የክርስቶስ አካልን ስሜት መጠበቁ ሁሉም እንዲታነጽ ያደርጋል። "በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፣ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል።...በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።" (1ቆሮ. 14:1፣ 4)

በቤተ ክርስቲያን ወይም በአካል ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ራስ ነው። ጌታ ኢየሱስ ራስ ከሆነ እኛ ደግሞ አካሎች ነን። ራስ የሚለውን ነገር ማዳመጥ መቻልና በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት ለአምልኮ ጣዕም ይሰጣል።

8. የጸጋ ስጦታዎችን በትክክለኛው ቦታ መጠቀም። የአምልኮ መሪ የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎች ሊኖሩት ይችላሉ። እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች በአግባብና በማስተዋል በሥራ ላይ ከዋሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይታነጽበታል፣ ያድግበታልም። "ቃሉም ሁሉም ለማነጽ ይሁን" ስለሚል የአምልኮ መሪ በይበልጥ መጠቀም ያለበት የጸጋ ስጦታ ለግል መታነጫ የተሰጠውን ሳይሆን ለጉባኤ ወይም ለኅብረት አገልግሎት በተሰጠው የጸጋ

ስጦታ ቢሆን ሁሉም በአንድነት ለአምላኩ የአምልኮ መሥዋዕትን ማቅረብ ይችላል። መሪ ጉባኤውን ሁሉ አዲሶችንም ሆነ በእግዚአብሔር ቤት የቆዩትን በአንድነት ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግባት ሃላፊነት አለበት። "... እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ቢገቡ አብደዋል አይሉምን? ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉም ይወቀሳል፣ በሁሉም ይመረመራል፤ በልቡ የተሰወረው ይገለጣል እንዲሁም፡- እግዚአብሔር በእውነት በመሃከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።" (1ቆሮ. 14:23-25) የአምልኮ መሪ ሃላፊነት ሁሉንም እዚህ ደረጃ ላይ ማድረሱ ላይ ነው።

**9. በመዘመርና በማስመለክ መካከል ያለውን ልዩነት** መገንዘብ። ድምጽ ያለው ሁሉ መዘመር ይችላል። ነገር ግን አምልኮን መምራት ከድምጽና ከሙዚቃ እውቀት በላይ ነው። አምልኮን መምራት ቀባት የሚያስፈልገው ራሱን የቻለ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

**10. የአምልኮ መሪ ራሱን ሆኖ መቅረብ።** የሌላ አምልኮ መሪን ዘይቤና ፎርም አጥንቶ እንደዚያ ሰው ጥሩ መሪ መሆን አይቻልም። ያ ሰው ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ በመስጠቱ ምክንያት የዚያን ሰው ባሕርያት ስላነሳለት ለእኛም እነኚያኑ ባሕርያት ያነሳልናል ማለት አይደለም። ሌላውን መሪ ለመምሰል ከመጣር ይልቅ ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ብንሰጠው ከጸጋው የተነሳ በሙላት ሊጠቀምብን ይችላል።